# የገበሬው ዋሶች..!

*ወንዶሰን*

የአርሶ አደሩ ህመም እኛንም ያመናል..
የገበሬው ቁስል ይጠዘጥዘናል፤....
ለአፈር ገፊው ስንል ቆስለናል ሞተናል..፤
ሲሉ የሚያቅራሩት እኚህ ነጻ አውጭዎች፤
የተገፉው ትውልድ ጠበቃው ነን ባዮች፤

ለምስኪኑ ወገን ለዚህ ለአርሶ አደሩ..
ለካንስ ! ለካንስ! ዋሶቹ ነበሩ...

በርሃብ ሲቆላ በጠኔ ሲታመስ...
ለወደቀ ጥሬ ሽሚያ ሲተራመስ፤
ሕጻን የናቱን ጡት - በድኑን አቅፎ ሲነክስ፤
ጠብታ ሲያጣበት - ምርር ብሎ ሲያለቅስ፤
የተመለከተው ለጋሱ የአለም ሕዝብ፤
የላከውን ዕህል የላከውን ገንዘብ፤
ተቀብለው ወስደው እነኚህ ታጋዮች፤
የሚስኪኑ አርሶ አደር ጠበቃና ዋሶች፤
ቅርጥፍ አርገው በልተው የህጻኑን ወተት፤
በስሙ ያገሱት...ሕጻን ማሙሽ ሲሞት፤
ለካንስ እውነትም ጠበቆቹ ናቸው፤
የገበሬው ህመም ቁስሉ ያመማቸው፤

ምና ባቱ እህል ምን አባቱ ወተት፥...
ጡት እንደነከሰ ማሙሽዬም ቢሞት፤
በድል አረፈ እንጂ መች ሞተ ይባላል፤
በስሙ የሚያገሱ ሺ መለስ ቀፍቅፏል፤
በጠኔ ተደፍቶ ሺ ቦርጭም አፍርቷል ፤

እንዲህ እንጂ ዜጋ - እንዲህ እንጂ ታጋይ፤
እርጥባኑን ዘርፎ - እጣን በራብ ገዳይ ፤
እንዲህ እንጂ ጀግና - ይሄ እንጂ ወንድነት፤
የህጻን ማሙሽን ምሱን ቀምተውት፤
እህል ባይኑ ሳይዞር በጠኔ ደፍተውት፤
በሰሌን ጠቅልለው አፈር አልብሰውት፤
ከመቃብር ቤቱ ታግለው ነጻ አወጡት፤

ዛሬ አፈር ቢጫነው እንዴት ይቆጨዋል?
በጠኔ ተደፍቶ ሺ ቦርጭም አፍርቷል ፤
በድል አረፈ እንጂ መች ሞተስ ይባላል፤
በስሙ የሚያገሱ ሺ መለስ ቀፍቅፏል።